DENVER PUBLIC SCHOOLS
Discover a World of Opportunity™

# ስለምዘናዎች ወይም ፈተናዎች የወላጆች መመሪያ

*ለ2018-19 የትምህርት ዘመን*

## NAEP (ብሔራዊ የትምህርታዊ ዕድገት/ለውጥ ምዘና)

ምዘናዎች ወይም ፈተናዎች ለተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለትምህርት ባለሙያዎች (አስተማሪዎች) ተማሪዎች የየክፍል ደረጃቸውን እውቀት (ይዘት) ስለማወቅ አለማወቃቸው እና ለ21ኛው መ/ክ/ዘ ዝግጁ ሆነው ለመመረቅ ስለመቻል አለመቻላቸው ጠቃሚ መረጃ ይሰጣሉ። የምዘና ውጤቶቹ የልጅዎ ትምህርታዊ ዕድገት/ለውጥ በጥቅሉ ከሚያሳዩት ምዘናዎች አንድ መለኪያ እንዲሆኑ የታሰቡ ናቸው።

## ይህ ምዘና/ፈተና ምንድን ነው?

ብሔራዊ የትምህርታዊ ዕድገት/ለውጥ ምዘና (NAEP) የሀገራችን ተማሪዎች እንደ ሒሳብ፣ ንባብ፣ ሳይንስ እና ጽሑፍ ያሉ ትምህርቶች ላይ የሚያውቁትን እና ማድረግ የሚችሉትን የሚመዝን በብሔራዊ ደረጃ ወካይ የሆነ ትልቁ ምዘና/ፈተና ነው። እንደ ዓመቱ ሁኔታ በቴክኖሎጂ ክህሎት እና በሶሻል ስተዲስ ላይ የሚያተኩሩ ምዘናዎች ሊሰጡ ይችላሉ። ውጤቶቹም በብሔራዊ የሪፖርት ካርድ መልክ ይሰጣሉ።

NAEP ከስቴት ምዘናዎች/ፈተናነት ባለፈ ሌላ አገልግሎትም አላቸው። ስቴቶች በተለያዩ የይዘት ደረጃዎች የየራሳቸው ልዩ ምዘናዎች አሏቸው። የተማሪዎችን ውጤታማነት በአንድ የጋራ መለኪያ ለመለካት እንዲቻል በእያንዳንዱ ስቴት ውስጥ አንድ ዓይነት የNAEP ምዘና ይሰጣል።

የዴንቨር የሕዝብ ት/ቤቶች ለብዙ ዓመታት በNAEP ውስጥ ተሳትፏል። በሙከራ የከተማ ክልል ምዘና (TUDA) በተባለው የNAEP ክፍል በሆነው ምዘና ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳተፍነው በ2016-17 የትምህርት ዘመን ነበር። ከ27 ሌሎች ዲስትሪክቶች ጋር እንደዲስትሪክት ከሌሎች ተመሳሳይ ዲስትሪክቶች አንጻር ያለንን አፈጻጸም በተሻለ ግንዛቤ ወይም መረዳት ይኖረናል። ከዚያም በቀላሉ ልንጠቀምባቸው የምንችላቸውን በሌሎች ዲስትሪክቶች ጥቅም ላይ የዋሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመረዳት መሞከር እንችላለን።

ወላጆች ልጆቻቸው ይህን ፈተና እንዳይወስዱ ለማድረግ መምረጥ ይችላሉ፤ ነገር ግን፣ ተማሪዎች በNAEP ሲሳተፉ እና የሚችሉትን ያህል ጥረት ሲያደርጉ በሞላ ሀገሪቱ የተማሪዎችን ውጤታማነት ሊገኝ ከሚችለው የተሻለ ትክክለኛ ልኬትን እናገኛለን።

## ልጄ የሚፈተነው/የምትፈተነው መቼ ነው?

**የፈተና መስኮት /Window/**
የፈተና/የምዘና መስኮት ልጅዎ የተወሰኑ ቀናት ላይ ፈተናውን የሚወስድበት/የምትወስድበት እና የተወሰኑ ሌሎች ቀናት ደግሞ መመሪያ የሚቀበልበት/የምትቀበልበት ክፍለ ጊዜ ወይም ወቅት ነው። ተማሪዎች በመስኮቱ ሙሉ ጊዜ ሁሉ ፈተና/ምዘና አይወስዱም። የሚሳተፉትም በአንድ የትምህርት መስክ ብቻ ነው። የልጅዎን ዝርዝር የፈተና ቀኖች ለማወቅ እባክዎ የልጅዎን መምህር ይጠይቁ።

NAEP የሚሰጥበት ወቅት (የጊዜ መስኮት) ከጃንዋሪ የመጨረሻ ሳምንት እስከ ማርች አጋማሽ ነው። ተማሪዎች በፈተናው በግምት ከ90 እስከ 120 ደቂቃ ያህል ይወስዳሉ።

## ልጄ ምን ውጤት(ቶች) ይሰጠዋል/ታል?

ውጤቶች ከፈተናው በኋላ በግምት በስድስት ወር ውስጥ ይገለጻሉ። ውጤቶች የሚገለጹት በጥቅሉ በዲስትሪክት ደረጃ ነው፤ የግለሰብ ተማሪ ወይም ት/ቤት ውጤት አይገለጽም።

## እነዚህ ውጤቶች እንዴት ጥቅም ላይ ይውላሉ?

ከዚህ ምዘና የሚገኘው መረጃ (ዳታ) መማር-ማስተማርን ለማሻሻል ባይጠቅምም የእኛ ተማሪዎች ከሌሎች ዲስትሪክት ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸሩ ያላቸውን አፈጻጸም ለመገምገም የተሻለ ልኬትን ይሰጣል። ከዚህ ምዘና የሚገኘው መረጃ:-

- እንደ 'ቴክኖሎጂ በተማሪ ትምህርት ውስጥ ምን ሚናን ይጫወታል' ያሉ የምርመር ጥያቄዎችን እንድንመልስ ሊያግዘን ይችላል።
- ለፖሊሲ ተንታኞች ተማሪዎቻችን ስኬታማ ለመሆን ምን ይፈልጋሉ ለሚለው የተሻለ መረዳት ሊሰጣቸው ይችላል።
- ለተማሪዎቻችን፣ በተለይም በታሪካዊ አጋጣሚ ዝቅተኛ ተገልጋይ ለሆኑ ተማሪዎች፣ ጥራት ያለው ትምህርትን እያቀረብን መሆን/አለመሆናችን እንድንረዳ ሊያግዘን ይችላል።
- ዲስትሪክቱ ተጠያቂ እንዲሆን ለማድረግ እንደመሣሪያ ሊያገለግል ይችላል።

## ? ተጨማሪ መረጃ

በልጅዎ ትምህርት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ እናበረታታዎታለን። ልጅዎን በቤት ውስጥ ማገዝ ስለሚችሉባቸው መንገዶች እና ሊገኙ ስለሚችሉ የፈተና እገዛዎች (አቅርቦቶች) ለመጠየቅ እንዳያመነቱ እባክዎ።

**ለተጨማሪ መረጃ:- ምዘናዎች**
የሚከተሉትን ድር ገጾች ይጎብኙ:-

- http://assessments.dpsk12.org
- http://nces.ed.gov/nationsreportcard/

ስለምዘናዎቹ ጥያቄዎች ወይም ሀሳቦች ካሉዎ፣ የልጅዎን ት/ቤት በቀጥታ ያነጋግሩ ወይም የቤተሰብ የምርጫ ክልል /Constituency/ አገልግሎትን በ(720) 423-3054 ደውለው ያነጋግሩ።